# ዴሞክራሲ

ስለዴሞክራሲ ብዙዎች ይናገራሉ ብዙዎች ይዘምራሉ። በዴሞክራሲ ስም ብዙዎች ይምላሉ። ብዝዎች ይገዝታሉ። ሁሉም የተናግሩለት የዘመሩለት የማሉበት የገዙቱበት ምን ያህል ወገን ሲሆንበት ይሆን? ወይምስ በፍቅር ያላበደ በፍቅር እንዳበደ እንደሚዘፍን ዘፋኝ፡ ያልሆነውን ሆኖና መስሎ ድራማ እንደሚሰራ ተዋናይ ስለሚሆኑ ይሆን? በነገራችን ላይ አንድ ሰው ያለተፈጥሮው መሆን ይችላልን? ይሔን ነገር አንባቢዎች የየብኩላቹህ አስተያየት ብትሰጡበት ተገቢውን መልስ ወይም አስተያየት ይገኝበታል ብየ እገምታለሁኝ። ከዚህ በመነሳት በበኩሌም ብሆን ቀጥየ እምለው ነገር ይኖረኛል።

አንድ ታሪክ ባጫውታቹህ በጣም ደስ ይለኛል፡ ታሪኩ በጣም ብዙ ግዜ ያስቆጠረ በመሆኑም ምክንያት 20 ዓመታት ወደኋላ ስመልሳቹህ ሁላቹህ ያንን ያህል ግዜ ተመልሳቹህ ያሳለፋቹህትን ሂወትና በየነበራቹበት ቦታና አካባቢ የነበረው የዛን ግዜ ሁኔታም ጭምር ትዝ እንደሚላቹህ እርግጠኛ ብሆንም፡ ምን ያህል አስደሳች ወይንም አሳዛኝ እንደነበረ በዛን ግዜ የነበረውን ሁላችን ሳናስታውስ አንቀርም። እኔ ጋ 20 ዓመታት ወደኋላ ተምልሳቹህ ያን ግዜ ያሳለፋቹህትም ይሁን ያያቹትን መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር ያ አሁን ታሪክ ሆነዋል። በዛን ግዜ የነበራቹህ ሆነ ወደዚቹህ ዓለም ከዛ በኋላ ለመጣቹህ ከዚህ ቀጥየ የማቀርበውን እውነተኛ ታሪክ ላካፍላቹህ። በታሪኩ ፍፃሜ ለነበራቹህ ደግሞ ታሪክን ለሚመለከተው የማስተላለፍ ግዴታና ሓላፊነት ስለሚኖራቹህ ግደታቹህንና ሓላፊንታቹህን እንድትወጡ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ሳላሳስባቹህ ማለፍ አልመርጥም።

ግዜው ጥር ወር 1982 ዓ/ም መሆኑ ነው። አከባቢው በጋይንት ጎንደር ክፍለ ሃገር ነው። በሰሜን ጎንደር በጃናሞራ ደረስጌ ማርያም ሰንቃበር ቦሃይት ደባርቅ ውቅን ዳባት እና አከባቢው በጣም ብቆይም፡ ጋይንትን ከገባሁኝ ግን የቀናት እድሜ ነበር የቆጠርኩት።

ጋይንት የደረስኩት ከነበርኩበት ክፍለ ጦር ጋራ ነው። ኣሉላ ክፍለ ጦር ይባላል። ኢህአዴግ በደርግ ደብረታቦርን ከተቀማ በኋላ፡ የደርግን እንቅስቃሴ በዛው ጠብቦ እንዲቀር በጉና ተራራ መሽጎ የተከላካይነት ውግያ ከጀመረ ቆይቶ ነብር ክፍለ ጦራችን ጋይንት ሲደርስ።

በዛን ግዜ ደርግ ብቻ አልነበረም የኢህአዴግ ጠላት። በህወሓት(ወያነ) ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው የአመለካከት ችግርም ሌላ ጠላት ሆኖ ህወሓት/ኢህአዴግን መዋጋት ጀምሮ ነበር። ይህ ጠላት ከደርግ በላይ ህወሓት/ኢህአዴግን አደጋ ላይ መጣል የሚችል ጠላት ነበረ። በዛን ግዜ ደርግ በትግራይ ውስጥ ያልነበረበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበረ። ቀደም ሲል ደርግ ከትግራይ ተጠራርጎ በራያ አከባቢ ብቻ በነበርበት ወቅት፡ 44,000 የትግራይ ወጣት ወደ ትግሉ(ህወሓት) የተቀላቀለበት ግዜ ነበር። ሆኖም ግን ትግሉ እንደጠበቀው ቀላል ሆኖ አልቆየውም። እንድያው በጣም ፈታኝ ሁኔታዎችን መከሰት ጀምረዋል። በተዋጊ የህወሓት ታጋዮች

ያልተጠበቀ ሁኔታ ተፈጠረ። በትግራይ በወሎ በጎንደር ከደርግ ጋራ ሲዋጋ የነበረውና ያለው የትግራይ ሰው ነው። ከኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች በሁሉም መስክ የተሻለና በወታሃደራዊ ዓቅሙና ልምዱ የበለጠ የህወሓት ታጋይ ነበረ። በህወሓት ውስጥ ከስምንት እግረኛ ተዋጊ ክፍለ ጦሮች በላይ ነበሩ። ከዚህ በመነሳት ከትግራይ ጀምሮ እስከ የመጀመርያው ደብረታቦርና ወረታ በነበረው ኣሰልቺና አስከፊ ጦርነቶች ኣመዛኙ ስራ የሰራው የህወሓት ታጋይ ነበረ። ይሔ ማንም ሊለውጠው የማይችል እውነተኛ ታሪክ ነው። ከዚህ በመነሳትም ነበረ ችግሩን የመጣው። ደርግ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት እንደምሆኑ መጠን ለምን ከዚህ በኋላ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግሉን ተቀብሎ ኣይጨርሰውም? ለምንድነው የውጭ ጠላት ቢመጣ ከማንኛው ኢትዮጵያዊ ህዝብ በላይ የሚሞተውና የሚጠቃው የትግራይ ህዝብ። የውስጥ ጠላትም ጋ እኛ ብቻ ለምን እንዋጋለን? ከዚህ በኋላ መሞት የለብንም። የሚል ከጠባብ ኣስተሳሰብ የመነጨ ጠላት ተፈጥሮ ነበረ።

የህወሓት ከላይ እስከታች ያሉ የኣመራር ኣካላት ይህንን ጠላት ከስር መሰረቱ የሚጠፋበት መላ መፍጠር ነበረበት። እንደዚሁ ጠላት ተይዞ መቆየቱ በድርጅቱ ኣሰራር ለተወሰነ ግዜ ቢይቻልም ወድኋላ ውጤቱ መጥፎ ሰለሚሆን፡ ደርግን እየተከላከልክ ጠበብተኝነትን ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ብቸኛ መፍትሔ መሆኑን ስለታመነበት፡ በህወሓት ታጋይ የኣስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ፖለቲካዊ ትግል ማካሔዱን ተመርጦ፡ እየተዋጋህ እየበላህ እየሰራሕ እየተሰበሰብክ ጠበብተኝነትን መመከት ተያያዝነው።

በዕርግጥ ቀላል ኣልነበረም ከ44,000 ህወሓትን የተቀላቀለ የትግራይ ወጣት ከዛ ጠባብ ኣመለካከት በመነሳት 33,000 ታጋይ ህወሓትን ትቶ የሸሸበት ግዜ ነበረ (ኣዲስ ትግሉን ከተቀላቀሉ ታጋዮች)። በተዋጊ ታጋዩ በኣመራር የነበሩ ጥቂቶች ቢሆኑም የዛን ሃሳብ ኣራማጆች ነበሩ። በዚ ኣስቸጋሪ ግዜ ህወሓት/ኢህኣዴግ ውጥረት ውስጥ በነበሩበት መጥፎ ግዜ በጥር 15/82 ጠዋት በጉና ተራራና ኣከባቢው የተለመደው የእንኳን ደህና ኣደራቹህ ተኩስ ተጀመረ። በየቀኑ የተለመደ ስለነበረ ለግዜው ብዙም የሚያሳስብ ነገር ኣልነበረም። ተኩሱ ባልተለመደው ሁኔታ ግን እየተራዘመ መጣ። የእኛ ክፍለጦር(ኣሉላ) ከደባርቅና ከዳባት እንደመጣን ወደ ጦርነት ወረዳ ለውግያ ብለን ባንሄድም፡ በጉና ተራራና ኣከባቢው የተጠናከረ የመከላከያ ወረዳ (ምሽግ) እንዲኖር ያህል የክ/ጦራችን ሬጅመንቶች በየተራ በየምሽቱ ምሽግን ያጠናክራሉ ይቆፍራሉ። በዛን ቀን ሬጅመንት መትከል ምሽግ እየቆፈረች ባደረችበት ጠዋት ነበር ተኩሱን የተከፈተባት። ቀጥሎ ግን በኣጠቃላይ በጉናና በኣከባቢው ከባድ ውግያ ተቀጣጠለ። የተቀረን የኣሉላ ክ/ጦር ታጋዮች በተለመደው የጸረ-ጠባብተኝነት የፖለቲካ ስራ ተሰማርተን ነበር የዋልነው። ለምሳ ከስብሰባ እንደወጣን እጃችን ታጥበን ለመብላት በየቦታው ቁጭ ብለን ስንጠባበቅ እያለን ገና ሳንበላ ተዘጋጅ የሚል ትእዛዝ ወረደ። ብዙም ሳንቆይ ወደ ጉና ተራራ መሮጥ ጀመርን። በተከታታይ የሚወርድ ትእዛዝ ፍጠን ፍጠን ተሎ በል የሚል ብቻ እንጂ ለማረፍ የሚያመች ሁኔታ ፍፁም ኣልነበረም። ጦሩነቱ ገና ጉና ተራራን ሳንደርስ ደርግ በክፍለ ጦራችን ላይም ጦርነት ኣወጀ። ሚጎች እኛ ጋ መደብደብ ተያያዙት። በሚጎቹ ምክንያት ሩጫችን መቋረጥ ኣልነበረበትም። የግድ ጉና ተራራ መድረስ ነበረብን። ይሬጅመታችን ታጋዮች ሁላችን ባንሆንም ብያንስ ሶስት ኣራተኛ ደርሰን ይሆናል። ይሔ በግምት ሳስታውሰው ነው። ከዛም

ሊያንስ ይችል ይሖናል። እንደማይበልጥ ግን እርግጠኛ ነኝ። ተሎ ብለን ጉና ተራራ የደረስን ታጋዮች ገና ላልደረሱ ታጋዮች እስኪደርሱ መጠበቅ የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም። ጉና ተራራ ደርሰን ለተጠጋን ታጋዮች ለ5 ደቂቃዎች ያህል በሬጅመንት የፖለቲካ መሪያችን ስንሰበሰብ ሌሎች የሬጅመንት አመራር የግዜያዊ አሰላለፍ ሁኔታ ለመንደፍ ተሰብስበዋል። የፖለቲካ መሪያችንም ንግግር ጀመረ። "ላልደረሱት ታጋዮች ለመጠበቅ ግዜው አይፈቅድም። ጉና ተራራ የነበረው ሃይላችን በአጠቃላይ ከቦታው ለቀዋል። ካለ ክ/ጦራችን በስተቀር የተቀሩት ክ/ጦርቻችን ደርግ በወሰደው ማጥቃት ተበታትነዋል። ምሽግን ሳይለቁ ውግያ ላይ ያሉ የኛው ሬጅመንት(መትከል)ና የመይደይ ክ/ጦር አንድ ሻምበል ብቻ ናቸው። ስለሆነም ክ/ጦራችን ጉና ተራራን የማስመለስ ሓልፊነት ተሰጥቶታል።

ሁሉም ታጋይ በእግረኛነት ይዋጋል። የአየር መቃወምያ፡ የሞርታር፡ የቢቴን ተኳሾች፡ አስተኳሾች የመጓጓዥያ አባላት፡ ሓኪሞች፡ ኦፕሬተሮች ሁላችን በእግራኛነት እንዋጋለን" ካለ በኋላ በዛን ሰዓት የሬጅመንታችን ኮማንደር(ወታሃደራዊ መሪ) አሰላለፋችን ከገለፀልን በኋላ በቀጥታ ጦርነቱን ጀመርን። በዛን ወቅት እኔ የሬጅመንት ሑመር ፐርሰነልና የሬጅመንቱ ስታፍ የሻምበል የአደረጃጀት ሓላፊ ነበርኩኝ። በተሰጠኝ አቅጣጫ ከአስር ታጋዮች ጋራ ስራችን ጀመርን። በዛን ሰዓት የነበረው ውጥረትና አስከፊ ውግያ ገላጭ ሓሳብ አሁን ማስቀመጥ ባልችልም ብያንስ አራት ወይም አምስት ክፍለጦሮች ይዘውት የነበረውንና በደርግ ቁጥጥር ስር የገባውን ምሽግ በአንድ ክፍለ ጦር ለማስመለስ ምንያህል ከባድ እንደሚሆን መገመትም ያስቸግራል። በአጠቃላይ በጣም ከባድ ነበረ ብየ ባልፈው ይሻላል። ስራውን ግን ተሰራ። ወደማምሻው ጉና ተራራ በቁጥጥራችን ስር ገብታ አደረች። ሌሎች ክ/ጦርቻችንም ተጠናክሮ አብረውን ውግያው ቀጠሉ። በዛን ግዜ የክፍለጦራችን ታጋይ ብዛት ከሌሎች ክ/ጦሮች የተሻለ እንኳን ቢኖር ከ1200 አይበልጥም ነበር።

ሌሎች ክ/ጦሮች ለምን በደርግ ጉና ተራራን ተቀሙ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ብዙ ነገሮች ምክንያቶች ቢቀመጡም ዋናው ምክንያት ግን ጠባብተኝነት ተስፋፍቶ ስለነበር ነው። ህወሓት ይህንን ችግር በተዋጣለት ቆንጆ የአማራር ስራ ሁሉም አልፎ በደብረታቦር ግንባር የነበረው ጠላት ለመደምሰስ በቅተዋል።

እዚህ አንድ መነሳት ያለበት ጥያቄ ያለ ይመስለኛል። ለምን የህወሓት አመራር ያንን ይህል ሰራ? ምንያህል ኢትዮጵያውነት ሲሰማው ነው? ህወሓትስ ጠባብ ቢሔርተኛ ድርጅት ይሆን? ለሚሉ ጥያቄዎች መልሱን ለአንባቢዎች መተው ይቀለኛል። ታሪክ የመናገር በታሩኩ አፈፃፀም የነበርነውና የፈፃሚዎቹ የእኔና በቦታው የነበሩ ግደታ ይሆናል። ፍርዱን ግን የእናንተ (የአንባቢዎች) ነው።

ይህንን ለመጻፍ ያነሳሳኝ ሌላ ጉዳይም ስለሆነ እላይ የገለጽኩት ከዋናው ጽሑፌ የተያያዘ ታሪክ ስለሚኖረው ነው እንጂ ቀጥተኛ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ዓላማ አይደለም። ከደብረታቦር ጦርነት በኋላ ህወሓት/ኢህአዴግ ለቀጣዩ ሌላው የኢትዮጵያ ምዕራፍ መዘጋጀት ስለነበረበት፡ ስራው ተጀመረ። ከደብረታቦር ጦርነት በኋላ የእኔ የስራ ሓልፊነትም በአዲስ ዘመን ከተማ ተቀየረ። የሻምበል የፖለቲካ ሓላፊ ሆንኩኝ። በየቀኑ ለእንመራው ሻምበል የአስተሳሰብና አመለካከት

ለውጦች የማምጣት ጉዳይ የእኛ ስራ ሆነ። ለተወሰኑ ወራት በየሁለት ሶስት ሬጅመንቶች ኣሰልቺ ስብሰባዎችና ወታሃደራዊ ስራዎች ተካሔዱ። ከዛን ስራ በኋላ በኣከባቢው ከነበሩ ክ/ጦሮች ኣሉላም ጨምሮ ወደ ሌላ ስራ ሲሰማሩ ለፖለቲካዊ ስልጠና የመቶ የፖለቲካ መሪዎች፡ የሻምበል የፖለቲካና የኣደረጃጀት መሪዎች ወደ ማሰልጠኛ ተላክን።

ከደብረታቦር ተነስተን ጋሳይ ክምር ደንጋይ ጉና ተራራን ወደ ኋላ በመተው ተጉዘን ንፋስ መውጫ ኩታበር ወረኢሉና ሌሎች የወሎና ደቡብ ወሎ ከተሞችን ኣልፈን ዋድላ ድላንታ ተንታ ከተማ ደርሰን ለግዜው ጉዛችንን ኣጠናቀቅን። ማሰልጠኛው እዛ በተንታ ከተማ መሆኑ ነው። በዛ ስልጠና ከተሳተፉ ታጋዮች ምን ያህል በሂወት እንዳሉ ኣላውቅም ከማሃል ሜዳ ተነስተን መዘዞና ሰላድንጋይ ለመቆጣጠር በተደረገው ውግያዎች ከክፍለጦራችን ሁለት የሻምበል የፖለቲካና የኣደራጃጀት ሓላፊዎች ተሰውተዋል (ከሞላሌ ተነስተን ሰላድንጋይ በተደረገው ውግያ)። ኣንዲት የሻምበል የፖለቲካ ሓላፊ ደግሞ ከክፍለ ጦር ኣቃቂ (ባሽ በተባለው ኣካባቢ)እንደተሰዋችና በደብረብርሃን ደግሞ ሌላ የሻምበል የፖለቲካ ሓላፊና በሻዕብያ ወረራም በ1982 ዓ/ም የሻምበል የፖለቲካ መሪ የነበሩ ሁለት ተሰውተዋል። ከዛ ውጭ የሌሎቹ ምንም እውቀት የለኝም። በዚህ ኣጋጣሚ ግን በስልጠናው የነበረ ካለ በፅሑፌን ማጠቃላያ ኢመይል ኣድራሻየን ስለሚኖር መገናኘት እንችላለን። የፅሑፌን ዋና ምክንያት የዛን ስልጠና ታሪክ ላጭውታቹህ ነው የፈለግኩት።

ግዜው የደርግ የበታችነት የኢህኣዴግ የበላይነት የታየበት ግዜ ነው። ይህ ደግሞ ኢህኣዴግ ደርግን ከስልጣን በሓይል ኣስወግዶ ስልጣን ለህዝብ የሚያስረክብበት ግዜ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል።

በስልጠናው የኣሉላ የኣቃቂና የኣግኣዚ ክፍለ ጦሮች ታግዮች ነበርን በቦታው የተገኘነው። በዛን ኣከባቢ የተዘጋጀውም ለሶስቱ ክ/ጦሮች ነበርና። ሌሎች ክፍለጦሮቻችንም በሌላ ኣከባቢ ተመሳሳይ ስራ ፈፅመዋል። ይህ ስልጠና ለሁላችን በዛን የኣመራር ደረጃ ለነበርነው ስለተዘጋጀ ሁሉም በየተራ ስልጠናው ወስደዋል። ስልጠናው ስለተለያዩ ጉዳዮች የሚዳስስ ነብረ። ለሁሉም ጉዳዮች የየራሳቸው መፃሕፍት ነብሯቸው። ከተዘጋጁት መፅሓፎች ጥቂቶቹ ለመጥቀስ

1) የሽግግር መንግስትና ህዝባዊ መንግስት
2) ስለ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ግንባታ
3) ስለ ፀጥታና ሰላም ማስከበር

የሚያወሩ መፅሓፍቶች ነበሩ። እዚህ ለመፃፍ ምክንያት የሆነብኝ ስለ የሽግግርና ህዝባዊ መንግስት በሚመለከት ነው። የሽግግር መንግስትና ህዝባዊ መንግስት በሚለው መፅሓፍ ከደርግ ውድቀት በኋላ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሁኔታ ነው የሚያወራው።

- ደርግ በኢህኣዴግ ከስልጣን ከወረደ በኋላ የሽግግር መንግስት መመስረት ኣለበት ይላል መፅሓፉ። (የሃገሪቱ የበላይ ፓርላማ)

- የሽግግር መንግስቱን መመስረት ያለበት በኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋራ ነው ይላል። (ኢዴሃቅ መኢሶን ኢህአፓ ኢዲዩ ኦነግ በወንጀል ላይ ያልተሰማሩ የደርግ ባለስልጣናት) የነበሩም ሆነ ሌሎች ድርጅቶችም ጭምር። ይላል መፅሓፉ። (የሃገሪቱ የበላይ ፓርላማ)

ይህ የተባለው ነገር በስልጠናው በጣም ኣከራካሪ ነገር ፈጠረ። በተለይ በኢህኣፓ ኢዴዩ በመኢሶንና በደርግ ባለስልጣናት። ሌሎች በኢትዮጵያና ህዝቦችዋ ላይ ጥፋት ላላደረሱ ድርጅቶች ቢመጡ ግን ተቀብለዋል። ኢህኣፓ ኢዴዩ ጋ ለብዙ ግዜ የሰላም ጥሪዎች በህወሓት ቀርቦላቸው ሳይቀበሉ ቀርቶ በህወሓት ላይም ጦርነት ኣውጆ ተዋግቶ ተሸንፎ ከትግል ዓለም የወጡ ድርጅቶች እኛ በከፈልነው መስዋእትነት በስልጣን ላይ የሚመጡበት ምክንያት ኣይኖርም የሚል ኣቋም ይዘን ተከራከርን። ይባስ ብሎ ከሽግግር መንግስት በኋላ ለሚኖረው ህዝባዊ መንግስት በህዝብ ምርጫ እንደሚወሰን፡ በምርጫው ኢህኣዴግ በኢህኣፓ ቢሸነፍ እንኳን ኢህኣፓ ኢትዮጵያን ያስተዳድራል። የሚል ነገር ነበር የሰማነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ኢህኣዴግን ትቶ ኢህኣፓን ከመረጠ የህዝቡን ስህተት ሳይሆን የእኛን ስህተት ነው የሚሆነው። ምክንያቱም እኛ ህዝብን ማሳመን ባለመቻላችን የሚመጣ ውጤት ነው የሚሆነው። ይህንን እንዳይሆን ድሮ በወታሃደራዊ ሓይል እንዳሸነፍናቸው ኣሁንም ጠንክረን በፖለቲካ ዓለሙን ለማስሸነፍ በሚገባ መዘጋጀት የእኛ ፈንታ ነው። የሚል ነበር በድርጅታችን የተማርነው።በዚህ መፅሓፍ ስንወያይ ከተጠበቀው ግዜ በላይ ነበር የወሰድነው። በመጨረሻ ሰልጣኙ ታጋይ ኣመነበት።

የድርጅታችን ኢህኣዴግ መነሻ ዴሞክራሲያዊነት ስለነበረው፡ ህዝብ የመረጠው ስልጣን ላይ መምጣት እንዳለበት፡ እየታገልን ያለነውም ህዝብ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ መሆኑንም፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን ከደርግ በምንም የማንለይ መሆናችንን በማመን በህወሓት/ኢህኣዴግ የቀረበልን ሙሉ በሙሉ ተቀበልነው።

ይህ ኣባባል በዛን ግዜ ከሰማይ የወረደ ኣዲስ ኣስተሳሰብ ወይንም ኣመለካከት ኣልነበረም። ከጥንቱ ህወሓት ሲመሰረት ዓላማው ኣድርጎ ትግል የጀመረበት ዋናው ምክንያት ያ ነበር። ኢህዴንና ኦህዴድም በተመሳሳይ።ሰልጣኙም ለዚህ ነበር ሲታገል የቆየው። ያልተዋጠለት ነገር ቢኖር ግን እንዴት ኢህኣፓ? እንዴት ኢዲዩ? እንዴት መኢሰን? እንዴት የደርግ ባለስልጣናት? ነበር ያሳሰበው። ምክንያቱንም እነዚህ በሙሉ ጠላት ሆኖ ተዋግቶናልና። ኢትዮጵያ ለጥፋት ዳርገዋልና። ህዝባችን እንዴት ጠላቱን እንዲመሩት እንፈቅዳለን? ቢመሩት ኣደጋ ላይ ይጥሉታል። እንደዛ ከሆነ ድሮውንስ ለምን መስዋእት መክፈል ኣስፈለገን? ከሚሉ ስጋቶች የመነጩ ነበሩ እንጂ የታገሉበት ዓላማ ስላላወቁ ኣልነበሩም። የህወሓት ዓላማ ገና ድርጅቱን ለመቀላቀል ማሰልጠኛ ስትገባ ኣውቀሐውና ኣምነህበት ነው የምትሰለጥነው።

ኢህኣዴግ ከድሮ የነበረው ኣሁንም ያለው ከእነ ዴሞክራሲያዊ ባህሪው ነው። ከድርግ ውድቀት በኋላ በተለያዩ ግዜያት ምርጫዎች ተካሂደዋል። በምርጫው የተሸነፉ በሙሉ የመሸነፋቸው ምክንያት ኢህኣዴግ ዴምክራሲያዊ ካለመሆኑ

የተነሳ ነው ይላሉ። ልብ በሉ በስልጠና በነበርንበት ግዜ (1982 ዓ/ም በተንታ ከተማ) የኢትዮጵያ ህዝብ ኢህኣፓን ቢመርጥ ያንን ለመሆን ምክንያት የሚሆነው የእኛ(ኢህኣዴግ) ስህተት ነው። ህዝብ ማሳመን ማቀፍ ባለምቻላችን የሚመጣ ውጤት ነው። ብለዋል ኢህኣዴግ ስያሰለጥነን። የኣሁንዎቹ ተሸናፊዎቻችን ግን ድክመታቸው ከመፈለግና ከማስተካከል ይንቅ ኢህኣዴግን ያወነጅላሉ። ይባስ ብሎ ደግሞ ሕገ-ወጥ ስራዎች ይሰራሉ፣ ረብሻ ያነሳሉ፣ ህዝብ ለህዝብ ያጋጫሉ፣ የኣገሪቱ ኢኮኖሚ ያቃውሳሉ ወዘተ………… መንግስት ለድርጊታቸው የመከላከል መብትና ሓላፊነት ስላለው በሕግ ይጠቃቸዋል፡ ለኣገሪቱ ደህንነት ሕጎችን ያወጣል። መንግስት ስራውን ሲሰራ ዴሞክራሲ የለም የሚወጡ ሕጎች ፀረ-ዴሞክራሲ ናቸው ይላሉ። ለመሆኑ ዴሞክራሲ ገደብ እንዳለበት ያውቃሉን? በማንኛው ዓለም በዴሞክራሲ የሚመሩ ኣገሮች ድርጅትም ሆነ ግለ ሰብ ሕግን ሲጥስ በሕግ እንደሚጠየቅ ሳያውቁት ቀርቶ ይሆን? ታድያ ሃገርን ለመምራት የህግ ኣስፈላጊነት የሕግ የበላይነት ካላወቁ ስልጣኑን ብይዙ ሕግ የሌላት ሃገር ልያደጓት ይሆን? ኣንድ ሓቅ ማስቀመጥ ተገቢ ይመስለኛል። ኣሁን በሌላ ስሞች (መጠርያዎች) ተጠቅሞ ድርጅቶች እንመራለን የሚሉ ሰዎች በሙሉ በኢህኣፓ በመኢሰን በደርግና ሌሎች ድርጅቶች የነበሩና በዛን ግዜ ተሸንፎ መታገሉን ያቆሙ ሃይሎች መሆናቸው የዘነጉ መሰለኝ።

ስንቶች ተኮላሽተው ካረንቋ ዘቀጡ
ስንቶች ተሸንፈው ከጎደናው ወጡ
ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነው
ነገም እንኖራለን ታሪክ ምስክር ነው!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

የተባለውን ለእነሱና ሌሎች የዛን ግዜ የትግልን መራራነት መቋቋም ኣቅታቸው ህዝብንና ሃገርን ለካዱ መሆኑን ቢገባቸው ምን ያህል ጥሩ ነበር። ያንን ግዜ ኣይቻልም ያሉት በየቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች እውን ሆኖ ታሪክ የመሰከረው ሓቅ ነው።እነሱ ግን ኣሁንም ኣንቀላፍተዋል። ኣንድ ሰው በተፈጥሮው ሰራተኛና ታታሪ ከሆነ ማንም ሰው ሊለውጠው ኣይችልም። የኛ ፖለቲከኞች ደግሞ ባህሪያቸው ማጭበርበር መዋሸት ያላደረጉት ኣድርገናል ባዮች ኣረ ሰለ እነሱ ምኑስ ተወርቶ ያልቃል። ምድጃ ቢለዋወጥ ወጥ ኣያጣፍጥም! ስምም ቢለዋወጥ ሌላ ባህሪ ኣይሰጥም! ብየ ባልፋቸው ይሻለኛል።

በሚቀጥለው የ2002 ዓ/ም ምርጫ ሰላማዊና ህጋዊ እንዲሆን የኢህኣዴግና የኢትዮጵያ ህዝብ ምኞትና ሓላፊነት ነው ብየ በፅኑእ ኣምናለሁ። ሰላማዊና ሕጋዊ የማድረጉን ፈንታ የኢህኣዴግና የኢትዮጵያ ህዝብ ሓላፊነት ነው። የሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የማጭበርበርና ሰላምን የመንሳት ስራ መስራት ብቻ ነው ችሎታቸው። ባህሪያቸው ነውና። ዴሞክራሲያዊ መንገድ ቢከተሉ ይሰበራሉና። ዴሞክራሲ ያስሸንፋቸዋልና። ዴሞክራሲ ይቆመጥጣቸዋልና። ምክንያቱም የዴሞክራሲ ወገኖች ኣይደሉምና።

እንግዲህ በምርጫው ግዜ በሃገር ውስጥ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሰላሙን በመመኘት ለሚቀጥለው ኣምስት ኣስር ዓመታት ወይም ከዛ በላይ ገደብ ለሌለው ዓመታት ኢህኣዴግ በስልጣን እንዲቆይ ተስፋ ኣደርጋለሁኝ። ኢትዮጵያ

ኣሁን ለደረሰችበት ዕድገት ያበቃና ለወደፊቱም ኢትዮጵያ ከድህነት ሊያወጣ የሚይችል ብቸኛው ድርጅት ኢህኣዴግ ብቻ ነውና። መስዋእት ከፍለን ሂወታችን ሰጥተን ኢትዮጵያን እናኖራታለን ያሉና የታገሉና የተሰው ልጆችዋ የገነቡት ድርጅት ነውና። የደምና ኣጥንት ውጤት ነውና። ኢትዮጵያን የሚበጅ ከሩቅ ማየት የሚይችል ድርጅት ነውና። ለብዙ ዓመታት የስራና ኣስተዳደር ልምድ ያለውና። መብቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ሌሎች ቢይመረጡ ውድቀት ነው። ይንን ግምት ኣይደለም። የህዝብን የበላይነትን ያልተቀበለ ቅንጅት ኣዲስ ኣበባ ባሸተፈበት ቦታ እንኳን መስራት ኣልቻለም እንኳን ኢትዮጵያን የምታክል ሃገርን ሊያስተዳድር። እንግዲህ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ ዕድሜ ዘር ግዜና ቦታ ኣያስፈልግምና መንቴንና ግዴታየን ከህፃንነት ዕድሜን ጀምሮ በሂወት እስካለሁኝ መወጣት ኣለብኝ። ሁላችንም ኣለብኝ። እኔ በሃገር ውስጥ ስላልሆንኩኝ ደግሞ ለታገልኩለት ሃገር ኣንዴም በምርጫ ኣለመሳተፌ የሚሰማኝ ሓዘን ወሰን የለውም።

*ሰላምና እድገት ለኢትዮጵያና ህዝብዋ!*
*ምንግዜም ኢህኣዴግ!*

ኣንባቢዎች ከፅሑፌ ያስፈልጋል/ይጠቅማል የምትሉት ነገር እንዳገኛቹህ ተስፋ ኣደርጋለሁኝ።

**ሃይለ/ ተጋዳላይ** gedlawi_zemen@y7mail.com